# ሴት ልጅዎትን በማስገረዝዎት ጥቅም አለው ብለው፡ያምናሉን?



## ስለ ሴት ልጅ ወጫዊ ብልትን ስለ መቁረጥ(FGM) ለወላጆች የሚሰጥ መግለጫ

NKVTS

በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ

ይህ በራሪ የተዘጋጀው፤ በዚህ በራሪ
መጽኄት የተዘጋጀው በኖርዌ በጥቃት
እና ስር የሰደደ ጭንቀት ጥናት ማዕከል
(NKVTS) ሲሆን፣ በራሪው በኤሌክትሮኒክስ
መረጃ በድረ ገጻችን www.nkvts.no ይገኛል

3ኛ.እትመት ተሸሽሎ የወጣው በ2019

በእትመት የተዘጋጁትን በራሪዎች ለማግኘት
በpostmottak@nkvts.no ኤሎትሮኒክ ደብዳቤ
(ኢ-ሜል)አድራሻ ጽፎ መዘዝ ይቻላል

2008-2011 ፤ መንግስት ግርዘትን ለመከላከል በአወጣው
መርሐ ግብር መሰረት የኖርዊጂያን የጥቃትና አእምሮን
አዛቢ አደጋ(ጫና) ጥናት ማእከል (NKVTS) ግርዛትን
በሚመለከት ዳሰሳን(ጥናትን) እንዲያካሂድ፤ እውቀትን
እንዲያሰራጭና በዚህ ዘርፍ ውስጥ አገልግሎት ለሚሰጡ
ባለሙያዎች ምክርን እንደያስፈላጊነቱ እንዲያቀበል ግርዘትን
በሚመለከት አጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባሮች
ስራ ላይ ለማዋል እንዲችል ብቃት ያለው ቡሔራዊ
ማእከል እንዲመሰርትና እንዲሰራ በማለት ሐላፊነት
ተሰጥቶል።

ዲዛይን/ ግንኙነት፡ ክርስቲን ኢስታድ እና ካሪ ጃቬር
ፒደርሰን

## ተጽዕኖውን እንዴት ይቋቋሙታል?

በዘልማድ ጠቃሚ ነው ብለው ሲያምኑበት የነበረውን ባህላዊ ልማድ ሰብሮ መውጣት አስቸጋሪ ነው። ሴት ልጅዎት እንድትገረዝ አንድ ሰው ጫና ቢያሳድርብዎት፣ ጫናውን ለመቃወም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።

በተጽዕኖ የተነሳ ተሸንፈው፣ ልጅዎትን ለግርዛትና ለጉዳት አሳልፈው አይስጧት። ይህ

የመረጃ በራሪ ከዚህ የሚከተሉትን ጉዳዮች ያስገነዝብዎታል

- በጫና የተነሳ ሴት ልጅዎትን እንዳያስገርዙ ይረዳዎታል
- ሴት ልጅዎትን እንዲያስገርዙ ጫና በሚገጥምዎ ጊዜ፣ ድርጊቱን ለመቋቋም የሚረዳዎትን ሀሳብ ያገኙበታል።



ሰውነታችን ያለ ምንም እንከን የተፈጠረ ነው

## ልጅዎት ለራሷ ሰውነት ባለቤት የመሆን መብት አላት

ሴት ልጅዎት መላ አካሏን እንድትጠብቅ ሊረዷት ይገባል።

ማንኛውም አይነት ኃይማኖት፣ ክርስትናም ሆነ እስልምና ወላጆች ከልጆቻቸው ጤነኛ አካል ላይ የአካልን ማስወገድ መብት እንዲኖራቸው አይፈቅድም ።

ማንም ወላጅ ልጁን የመጉዳት ፍላጎት የለውም። በግርዛት ምክንያት በሴት ልጆች ላይ ለሚመጡ ችግሮች፣ በቂ የሆነ እውቀት ወላጆች ካገኙ የባህል ተጽዕኖውን መስበር ይችላሉ።

*ሁሉም ወላጆች ለልጆቻቸው መልካም ወላጆች መሆንን ይሻሉ።*



## የሚደረግብዎትን ተጽዕኖ ለመቋቋም እርዳታ ካስፈለገዎ፣ ከዚህ የሚከተለውን ማድረግ ይችላሉ።

- ግርዛትን በጽናት የሚቃወሙ ሰዎችን ያነጋግሩ
- ከሚያምኑት ጓደኛዎ ጋር በመወያየት፥ ጓደኛዎት ቤተሰብዎ እንዴት ተጽዕኖውን ለመቋቋም እንደሚችል ርዳታ ይለግስዎት።
- ወደ ትውልድ አገርዎ ሴት ልጅዎትን ይዘው ለጉብኝት በሚሄዱበት ወቅት ቅድመ ጥንቃቄ ያድርጉ።



## ሴት ልጅዎት እንድትገረዝ የሚገፋፉዎት ሰው ካለ፣ እንዲህ በማለት ይመልሱለት።

- ልጄን እንድትሞት ወይም በከባድ ሕመም እየተጠቃች ሕይወቷን በሙሉ እንድትኖር ለአደጋአላጋልጣትም።
- እኔ በኖርዌ ወጉን/ባህሉን ለማምለጥ አንድ እድል አግኝቻለሁና ። ስለዚህ እቓቓመዋለሁ።
- የሰው ልጅን ሰባአዊ መብቱን አከብራለሁ።
- ወንጀላዊ ድርጊትን መፈጸም አልፈልግም።
- በማረሚያ ቤት ውስጥ የመታሰር አደጋ እንድጋለጥ አልፈልግም። በመታረሚያ ቤት ከታሰርኩ ግን ቤተሰቤን መርዳት አልችልም።
- ልጄ አድጋ፣ አንድ ቀን  የወቀሳ አደጋ ላይ እንድደረስ እረሴን ማጋለጥ አልፈልግም።
- ልጄ በራስዎ ሰውነት/ገላ ላይ እንድትወስን እፈልጋለሁ።
- እኔ ለልጄ ምንም የማይወጣለትን የተስተካካለ ገላ ወይም ሰውነት የሰጣትን እግዚያብሔርን(አላሕህን) አከብራለሁ።
- .እኔ ለልጄ ማንኛውም ጥሩ የሆነ ደንብ ወይም እሴቶችን መስጠትና እንደዛም ብሎ ጥሩ፤መልካም

  ሰው እንድትሆን እፈልጋለሁ።
- እኔ ልጄ አንድ በአጠቃላዩ ለሷ ሙሉ ዋጋና ክብር የሚሰጣትን እና ከሷም ላይ ምንም ነገርን ማስወግድንም የማይፈልግ ባል እንድታገባ እፈልጋለሁ።
- እኔ ከዚህ ደንብ በስተቀር የተወለድኩበት አገሬንና ባሕሌን እወዳለሁ ።
- ግረዘት በ25 የአፍሪካ አገራት የተከለከለ ነው።
- 30 የአፍሪካ አገሮች ግርዘትንና ሌሎች ጎጂ ደንቦችን ለመቅረፍ(ለማስወገድ) ቢሔራዊ ኮሚቴዎችን መስረተዋል።
- የግረዘት ልምድ በአለበት አገራት ሁሉ ግረዘትን በማውገዝ በዙ ስራ እየተሰራ ነው።

## የኖርዌይ መንግሥት የህጻናትን ግርዛት ለመከላከል ድርጊቱን የሚፈጽሙትን አካሎች ህግን እንደጣሱና ቅጣቱም በይርጋ ወይም በጊዜ መራዘምም ቢሆን በወንጀሉ እንደሚጠየቁና ድርጊቱም ሊያስቀጣም እንደሚችል ህጉ ያስገነዝባል።

### ህጉ

ማንኛውም የሴት ልጅ ውስጣዊ ብልት መቁረጥ ድርጊት መፈጸም በህግ ያስቀጣል።
ቅጣቱም እስከ 6 ዓመት ድረስ በእስራት ነው። ሆኖም ድርጊቱ የተፈጸመባት ሴት ዘላቂ የሆነ በሽታ ላይ ከወደቀች ወይንም ማንኛውንም ስራ የማከናወን አቅሞን ለዘለቄታው ከአጣች፣ ለመዳን ለማይችል አደጋ ፣ስህተት ፣ ሞት፣ ወይም አቢይ የሆነ የአካል ጉዳት ወይም ጤናዊ ጉዳት ቢደርስባት ይህ ድርጊት እንደ ከፍተኛ ደረጃ ያለው የሴት ውጫዊ ብልት መቁረጥ ድርጊት ይታያል። ቅጣቱም ታዲያ በዛው መጠን እስከ 15 አመታት ይሆናል። (የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቅጽ 284 እና 285 (§§ 284 og 285)።

ጥቃት ያደረሰው አካልና ተባባሪውም ሰው አብሮ ይቀጣሉ።
ማንኛውም አይነት ግርዘት– "ሱና" ግርዛትንም ጨምሮ ጎጂና የተከለከለ ነው።

## የይርጋ (የጊዜው መርዘም የማያግደው) የህግ ተጠያቂነት

- ልጅዎ 38 አመት እስኪሆናት ድረስ ልትከሶ ትችላለች

ሕጋዊው የወላጅነት ሀላፊነት ልጃገረዶ 18 አመት ሲሞላት ያበቃል። ከዛ በሁአላ ከተገረዘች 10 አመት አላት(ድርጊቱ የሴትን ውጫዊ ብልትን መቁረጥ ነው ከተባለ) ወይም 20 አመት (ድርጊቱ ከባድ የሆነ የሴትን ውጫዊ ብልትን መቁረጥ ነው ከተባለ) ወላጆቿን ለመክስ ፍላጎት ከአላት በቂ የመወሰኛ ጊዜአቶች አሉአት። ይህ ማለት ሴት ልጁ ለግርዛትዎ በሕጋዊ መንገድ አላፊነት ያለው ተጠያቂ ሰው ልታደርጎት ትችላለች።





በራስዎት ባህልና በማንነትዎ ኮርተው ግን ጎጂ ባህሎችን ይስዋግዱ።

## ሴት ልጅዎን ማስገረዝ አያዋጣም ፤ ምክነያቱም

- ልጅትዋ ምንም አይነት አደጋ ቢደርስባትና ጤናዊ፤ስነአምሮአዊ ወይም ማሕበራዊ ችግር ቢያግጥማት ለችግሩ ተጠያቂ ልትሆኑ ይችላሉ። ሴት ልጅዎት መላ አካሏን እንድትጠብቅ ሊረዷት ይገባል።
- ልጅትዋ አድጋና ከስዋ ላይ ምንን እደወሰዳችሁባት ስትገነዘብ በቤተሰቡ ውስጥ መከፋፈልና ግጭቶችች ሊከሰቱ ይችላል። የሚያጋጥማችሁን የአካባቢ ጫና ለመወጣት እንድትችሉ እርዳታን ጠይቁ።
- ሕግን የመተላለፍ ሚስጥር ተሸክመው መኖር ይኖርቦታል። በኖርዌ ሕግ መሰረት የሴት ልጅ ግርዛት ወንጀል ነው። በመታረሚያ ቤት ውስጥ ከአሉ ቤተሰብውን መርዳት ይሳኖታል።
- ልጃችሁም እናንተ ወንጀላዊ ድርጊት የመፈጸማችሁን ሚስጥር ተሸክማ መኖር ይኖርባታል። ለልጅዎ መልካም የሆነውን ማድረግ የርሷ ሐላፊነት ነው። በራሷ አካል ላይ መወሰን እንድትችል እርዷዋት።



ልጅዎት አካሏን እንድትከላከል ይርዷት



## በባሕልሽ የምትኮሪ ሁኚ

በራስ መተማመንን አግኝተሽ ያንችን ማንነት በበሕላሽ ከሚገኙት አወንታዊ ገጾች ዙሪያ ገንቢ። ግርዘት ጎጂ ፤ አላስፈላጊና ሕግ ወጥ ድርጊት ነው። በባሕልሽ ውስጥ የሚገኙትን ጤናማና ቀና(ጠቃሚ) የሆኑቱን ባህሎቸሽን አክብሪና ጠብቂ።

ከልጆችሽ ጋር እሴቶችንና ግብረ ገብነትን የሚመለከት አነስተሽ ተወያይ። ልጆሽን በበቂ ምክነያት የተደገፈን ግብረ ገባዊ ምርጫወችን እንዲወስዱና ጨዋ ሰው ለመሆን ብቃት እንዲኖራቸው አስተምሪያቸው።

ልጆዎት ቀዶ ጥገና ከአስፈለጋት እርዳታዎትን መለገስ ይገባዎታል ብሎም የሚስቸግራትን የጤናዊ ችግሮችን መላቀቅ እንድትችል።

ክብር ያላት ሴት ለመሆን የተገረዘች መሆን አያስፈልጋትም።

---

## ከዚሕ በታች የሚገኙትን ድርጅቶች ማነጋጋር ይችላሉ ማለትም እርዳን ወይም የሚያወያይዎ አካል ከአስፈለገዎት።

የቀይ መስቀል ሰልክ ቁጥር- ስለ የተገዶሽ ጋበቻና የሴት ውስጣዊ ብልት መቁረጥ ድርጊትን በሚመለከት
በስልክ ቁጥር 815 55 201

የተገዶሽ ጋብቻ፤ የሴት ውስታዊ ብልት መቁረጥ ድርጊትና አሉታዊ የሆነ ማሕበራዊ ቁጥጠር ተቃውሞ ብቃት ያለው ብድን። በስልክ ቁጥር 47 80 9050

አማትሄአ)፣ www.amathea.no ስልክ ቁጥር 815 32 005

SEIF (የስደተኞችና የውጭ አገር ሰዎች እራስን መርጃ ድርጅት)፣ በኦስሎ፥ትሮንድሃይም፥ አለሱንድ፥ ክርስትያንሳንድ፥ እና በርገን ቢሮ አለው፣ ስልክ ቁጥር 22 03 48 30።

PMV (ፕሪማርሜዲሲኒስክ ቨርክስቴድ) ድሕረ ገጽ https://kirkensbymisjon.no/pmv-flerkulturelt-ressurssenter-i-oslo/, ስልክ ቁጥር 230 60 380.

Tverrkulturell Helseinfo (THI) http://tverrkulturellhelse.info/ የተለያዩ ባህሎችን የዘለ የጤና መግለጫ (THI)

ዞናዊ የጥቃት እና ስር የሰደደ ጭንቀት ጥናትና የራስን ሕይወት የማጥፋት ተከላካይ ማዕከል(RVTS)
ድሕረ ገጽ, RVTS- ምእራባዊ ስልክ ቁጥር 55 97 66 95, RVTS ምስራቃዊ, ስልክ ቁጥር 22 58 60 00, RVTS መአከላዊ, ስልክ ቁጥር 72 82 20 05, RVTS ደቡባዊ ስልክ ቁጥር 22 58 60 00, RVTS ሰሜናው ስልክ ቁጥር 77 75 43 80

---

## ህጻናትን የአካሎቻቸው ባለቤት እንዲሆኑ ይርዱዋቸው።



NASJONALT KUNNSKAPSSENTER
**OM VOLD OG TRAUMATISK STRESS**

kjonnslemlestelse.nkvts.no